# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

## በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች /የኮንደሚኒየም / አሰጣጥ

## መመሪያ ቁጥር 28/2013

# ማውጫ


ይዘት ገፅ

መግቢያ ....................2

ክፍል አንድ ....................3

ጠቅላላ ድንጋጌዎች....................3

1. አጭር ርዕስ....................3

2. ትርጓሜ ....................3

3. ወሰን ....................4

4. የመመሪያው መርሆዎች ....................5

ክፍል ሁለት ....................5

የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዓይነት እና የአሰጣጥ ሁኔታ....................5

5. የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንደሚኒየም/ ዓይነት....................5

6. የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንደሚኒየም/ ተጠቃሚዎች እና የተጠቃሚነት እድል ....................5

7. የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንደሚኒየም/ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ መስፈርቶች....................6

8. የእጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ....................6

9. የኮንደሚኒየም የመኖሪያ ቤቶች እርክክብ ....................7

10. ለሌላ አካል ማስተላለፍን በተመለከተ ....................7

11. የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንድሚኒየም/ ተጠቃሚዎች መብቶች እና ግዴታዎች....................7

ክፍል ሶስት ....................10

ስለ ቅሬታ አቀራረብ ፣ ተጠያቂነት እና ሥራ ላይ ስለመዋል....................10

12. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ....................10

13. ተጠያቂነት....................10

14. የመተባበር ግዴታ ....................10

15. ስለትርጉም አሰጣጥ....................10

16. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች....................10

17. መመሪያውን ስለማሻሻል....................10

18. መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ....................10

## መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማን ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን ሲባል በተካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ምክንያት በግብርና ሥራ እየተዳደሩ ከሚኖሩበት አካባቢ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው ያለ በቂ ካሳ  ከይዞታቸው እንዲለቁ ሲደረግ የኢኮኖሚ ተጎጂ እንዳይሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ለከተማ አስተዳደሩ ብሎም ለሃገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ እድገት ሲባል በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ የተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸዉን ማሳደግ ተገቢ መሆኑ በመታመኑ፤

የከተማ አስተዳደሩ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ የተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮች ይዞታቸውን በማጣታቸው የመኖሪያ ቤት ችግር ተጠቂዎች እንዳይሆኑ ተገቢውየመንግስት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

በከተማ አስተዳደሩ አማካኝነት ለከተማዋ ልማት ሲባል የልማት መብታቸው ሳይጠበቅላቸው ከይዞታቸው ለተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮቹ እና ቤተሰቦቻቸዉ ከደረሰባቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር እንዲወጡ ለማስቻል እና ያሉባቸውን የመኖሪያቤት ችግር ለመፍታት በከተማ አስተዳደር የተፈቀዱ 22,915 የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በፍትሃዊነት፣ በግልጽኝነት  እና በትክክለኛ ህጋዊ አሰራርን እና የአርሶ አደሮችን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ መስጠት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 (3) (ሠ) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለተፈናቀሉ ተነሺ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች /የኮንደሚኒየም/ አሰጣጥ የወጣ መመሪያ ቁጥር 28/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ነው፤
3. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮምሽን ነዉ፤
4. **"ኮሚሽነር"** ማለት ኮሚሽኑን ለመምራት በሚመለከተው አካል የተሰየመ የበላይ ኃላፊ ነው፤
5. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በኮሚሽኑ ሥር የሚገኝ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ማለት ነው፤
6. **"በልማት ምክንያት የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ በግብርና ስራ ተግባር ላይ ኑሮውን መሠረት አድርጎ እየኖረ የነበረ እና እየኖረ ያለ ለልማት ሥራዎች ሲባል ከይዞታው የተነሳና የመሬት ይዞታውን የለቀቀ አርሶ አደር ሲሆን ቤተሰቦቹን የሚያጠቃልል ነው፤
7. **"አርሶ አደር"** ማለት በከተማዉ አስተዳደር ክልል ዉስጥ የሚኖር በግብርና ይዞታ መሬቱ ላይ በሚሰራዉ የግብርና ስራ በሚያገኘው ገቢ እራሱንና ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ሰው ነው፤
8. **"የአርሶ አደር ቤተሰብ "** ማለት በአርሶ አደሩ ስር እየተዳደረ ያለውን የአርሶ አደሩን ልጅ፣ ሚስት ወይም ባል ነው፤

9. **"ልየታ"** ማለት በከተማው አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በተዘጋጁ ፕሮጀክቶች እና የስራ ዕድሎች በመጠቀም መልሶ በማቋቋም ተጠቃሚ የሚሆኑ አርሶ አደርና የአርሶ አደር ቤተሰቦችን የመምረጥና የማደራጀት ሂደት ነው፤

10. **"ተጠቃሚ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ተፈናቅለዉ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግር የተጋለጡ ተጎጂዎች እና በቀጣይ በልማት ምክንያት ተነሺ የሚሆኑ አርሶ አደሮች እና የአርሶ አደር ቤተሰቦች ናቸው፡፡

11. **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት ከስራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው እና ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ ተጠቃሚዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ ነው፤

12. **"የጋራ መኖሪያ ቤት /ኮንደሚኒየም/ "** ማለት ለመኖሪያ ቤትነት አገልግሎት እንዲውሉ በከተማ አስተዳደሩ አማካኝነት ተገንብተዉ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ ለተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦች እንዲሰጡ ውሳኔ የተሰጠባቸዉ እና ለኮሚሽኑ የተላለፉ ባለ ሦስት፣ባለ ሁለት እና ባለ አንድ መኝታ ክፍል ያላቸዉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች /የኮንደሚኒየም / ማለት ነዉ፤

13. **"እጣ"** ማለት የጋራ መኖሪያ ቤቶችን /የኮንደሚኒየም/ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉን ለተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦች ያለምንም አድሎ ኮምፒተራይዝድ በሆነ መልኩ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች ለይቶ ለመስጠት እንዲቻል የተመረጠ የጋራ መኖሪያ ቤት አሰጣጥ ዘዴ ነዉ፤

14. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

## 3. ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ ለተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸዉ እንዲሰጡ በተፈቀዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች /የኮንደሚኒየም/ ላይ እና የቤቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተለዩ ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው መርሆዎች

1. መስራት የማይችሉ እና ምንም ገቢ የሌላቸዉ ተብለዉ የተለዩ በእጣ አወጣጥ ሂደቱ ቅድሚያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤
2. ግልጽኝነትና ተጠያቂነትን ተግባራዊ ማድረግ በሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መሰረት በዚህ መመሪያ በተዘጋጀ እጣ ማዉጫ ዘዴ ብቻ ተጠቃሚዎች የሚደርሳቸዉን ቤት በእጣ ብቻ እነዲያገኙ ይደረጋል፤
3. በዕጣ የሚሰጡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የተጠቃሚ አርሶ አደሮችን አሁን ያሉበት የመኖሪያ አካባቢ ከግንዛቤ ዉስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዓይነት እና የአሰጣጥ ሁኔታ

## 5. የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንደሚኒየም/ ዓይነት

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ባለ ሦስት መኝታ ቤት ፣ባለ ሁለት መኝታ ቤት እና ባለ አንድ መኝታ ቤት ተብለዉ ከከተማ አስተዳደሩ በልማት ምክንያት ለተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸዉ እንዲሰጡ ተለይተዉ ዝርዝራቸዉ ለኮሚሽኑ የተሰጡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ናቸዉ፤

## 6. የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንደሚኒየም/ ተጠቃሚዎች እና የተጠቃሚነት እድል

1. የጋራ መኖሪያ ቤት /ኮንደሚኒየም/ ተጠቃሚ የሚሆኑት በምዝገባ፣ ልየታ እና መረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 001/2009 መሰረት የተመዘገቡ እና የተለዩ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ የተፈናቀሉ ተጎጂ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸዉ ናቸዉ፤
2. በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ለጋራ መኖሪያ ቤት እጣ ውድድር ዉስጥ በአባወራ ፣በእማወራ እና የአርሶ አደር ቤተሰብ ሆነዉ እድሜአቸዉ 18 ዓመት እና በላይ የሆኑ እንዲሳተፉ ይደረጋል፤

3. በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 1. የተጠቀሰዉ ቢኖርም በጋራ ለሚኖሩ አባወራ እና እማወራ ከአንድ በላይ የመኖሪያ የቤት እድል ተጠቃሚ መሆን አይችሉም፤
4. በልማት ምክንያት ከይዞታዉ የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር ቤተሰብ ሆነዉ ትዳር መስርተዉ በጋራ የሚኖሩ ከሆነ ከአንድ በላይ የመኖሪያ ቤት እድል ተጠቃሚ መሆን አይችሉም፡፡

7. የጋራ መኖሪያ ቤቶች /ኮንደሚኒየም/ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ መስፈርቶች

1. በልማት ምክንያት ከይዞታዉ የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር እና ቤተሰቦቹ በምዝገባ እና ልየታ ሂደት ዉስጥ ያለፉ፤
2. በልማት ምክንያት ከይዞታዉ የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር አባወራ /እማወራ ስር በቤተሰብ አባልነት የተመዘገበ እድሜዉ ከ18ዓመት እና በላይ የሆነ፤
3. የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ፤
4. የጋብቻ ሰርተፍኬት (ያላገባ ከሆነ 6 ወር ያልሞላው ወይም የታደሰ)፤
5. የተፈረመ የግዴታ ውል፤
6. በዘህ መመሪያ የተቀመጡ የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታዎችን ለማክበር በፊርማዉ የሚያረጋግጥ፡፡

8. የእጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተለዩ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸዉ በተዘጋጀዉ ኮምፒተራይዝድ በሆነ የእጣ አወጣጥ ሥርዓት መሰረት የመኖሪያ ቤቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል፤
2. በዘላቂ ቀጥታ ድጋፍ የተመዘገቡና የተለዩ አባወራዎች /እማወራዎች በጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንደሚኒየም/ የባለ ሦስት መኝታ ቤት በመጀመሪያ እና በአንደኛ ወለል ላይ በቅድሚያ በዕጣ እንዲያገኙ ይደረጋል፤
3. ከዘላቂ ድጋፍ ተጠቃሚዎች የሚተርፉ የባለ ሦስት መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤቶች /የኮንደሚኒየም/ ከዘላቂ ድጋፍ ተጠቃሚ ዉጭ ላሉ ለሌሎች አባወራ እና እማወራዎች በዕጣ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

4. ከሁሉም አባወራዎች/እማወራዎች የሚተርፉ የባለ ሦስት መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤቶች /የኮንደሚኒየም/ እድሜአቸዉ ከ18ዓመት እና በላይ ለሆኑ በዕጣ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

5. ቀሪ ባለሦስት መኝታ ቤቶች እና ባለሁለት እና ባለአንድ መኝታ ቤቶች እድሜአቸዉ ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ በልማት ምክንያት ከይዞታዉ የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር ቤተሰቦች በእጣ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

9. የኮንደሚኒየም የመኖሪያ ቤቶች እርክክብ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ከኮምሽኑ ጋር በመቀናጀት በሚያዘጋጁት ፕሮግራም መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

2. በአንቀጽ 9 በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የተጠቃሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በልማት ምክንያት የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር ወይም ቤተሰብ የሚሰጠዉን የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንደሚኒየም/ በእጣዉ መሰረት በስሙ እርክክብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

10.ለሌላ አካል ማስተላለፍን በተመለከተ

1. ማንኛዉም የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንድሚኒየም/ የተሰጠዉ በልማት ምክንያት የተፈናቀለ ተነሺ አርሶ አደር ወይም ቤተሰብ  ቤቱ ከተሰጠዉ እለት ጀምሮ እስከ  አስር ዓመት ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ለሌላ አካል በማንኛዉም መንገድ ማዛወር አይችልም፤

2. በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንድሚኒየም መኖሪያ ቤት የተሰጠዉ የልማት ተነሽ አርሶ አደር ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ከሆነ በህግ የመዉረስ መብት ያላቸዉ የቤተሰብ አባለት ሊወርሱና በስማቸዉ ሊያዞሩ ይችላሉ፡፡

11.የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንድሚኒየም/ ተጠቃሚዎች መብቶች እና ግዴታዎች

1. የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንድሚኒየም/ ተጠቃሚ የሚሆኑ በልማት  ምክንየት የተፈናቀሉ ተነሺ  አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦች መብቶች፡፡

ሀ. አርሶ አደሩ የተሰጠዉን ቤት ለተፈቀደለት ዓላማ ወይም አገልግሎት የመጠቀም፤

ለ. አብረዉ ከሚኖሩ ሌሎች ነዋሪዎች ጋር በመቀናጀት የህንጻዉን ደህንነት ለመጠበቅ በሚያስችል መልኩ ለዉል ሰጭ እና ለሚመለከተዉ የመንግስት አካል በማሳወቅ እድሳት እና ጥገና የማድረግ፤

ሐ. በአካባቢዉ በተዘረጉ መሰረተ ልማቶች በአካባቢዉ ካሉ ነዋሪዎች ጋር እኩል ተጠቃሚ የመሆን፤

መ. በአካባቢዉ ነዋሪዎች በሚቋቋሙ ማህበሮች፣ እድሮች ወ.ዘ.ተ. የመደራጀት፤

ሠ. በአካባቢዉ በሚካሄዱ ልማቶች እኩል ተሳታፊ እና ተጠቃሚ የመሆንመብት አለዉ፡፡

2. **የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንድሚኒየም/ ተጠቃሚ የሚሆኑ በልማት ምክንየት የተፈናቀሉ ተነሺ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦች ግዴታዎች፡፡**

ሀ. ኮሚሽኑ በማንኛዉም ጊዜ ከተጠቃሚዉ መረጃዎችን ሲፈልግ በወቅቱ የመስጠት እና ለሚነሱ ጥያቄዎች ተገቢዉን ምላሽ የመመለስ፤

ለ. አርሶ አደሩ የሚሰጠዉን ቤት በተቀመጠው የማስተላለፊያ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ቀርቦ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀዉ ዉል መሰረት ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ እና ፈርሞ የመረከብ፤

ሐ. የተረከበውን ቤት በጋራ ህንጻ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የመጠቀም፤

መ. በተረከበው ቤትና የጋራ መጠቀሚያ ላይ ህገ-ወጥ ግንባታዎች ከማከናወንም ሆነ ግንባታ የማፍረስ ስራዎችን ከመስራትና ማንኛዉንም በዲዛይኑ ከተቀመጠዉ ውጭ ውስጣዊም ሆነ ዉጫዊ የቅርጽ ለውጥ ያለማድረግ፤

ሠ. የውሃና መብራት ቆጣሪዎችን በስሙ ለማዞር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸዉን የማስፈጸም ስራዎችን የመከታተልና የማስፈጸም፤

ረ. ተጠቃሚዉ በልማት ምክንያት ይዞታዉን የለቀቀ አርሶ አደር ስለመሆኑ እና በሥሩ የሚተዳደሩ ቤተሰቦቹ እድሜአቸዉ ከ18 ዓመት በላይ ስለመሆናቸዉ ወ.ዘ.ተ. የሰጣቸዉ መረጃዎች /ማስረጃዎች/ የተጭበረበሩ ወይም የተሳሳቱ

ማስረጃዎች ሆነዉ ከተገኙ የተረከበዉን የኮንደሚኒየም መኖሪያ ቤት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለዉል ሰጭ የማስረከብ፣ ተረክቦ ለኖረባቸዉ ወራቶች ዉል ሰጭ በሚያወጣዉ የቤት ክራይ ተመን መሰረት የመክፈል እና ለሰጠው የተሳሳተ መረጃ በህግ ተጠያቂ የመሆን፤

ሰ. ከአካባቢዉ የኮንድሚኒየም ነዋሪዎች ጋር በመደራጀት አካባቢዉን የማልማት እና ለኑሮ ተስማሚ የማድረግ እና የመጠበቅ፤

ሸ. በጋራ መኖሪያ ቤቶች /በኮንደሚኒየም/ ነዋሪዎች ማህበር አማካኝነት የሚወጡ መመሪያዎችን የማክበር እና የማስከበር፤

ቀ. በህንጻዉ ደህንነት ላይ ተጽኖ ከሚያደርሱና የአካባቢዉን ነዎሪዎች የእለት ተእለት ኖሮአቸዉን ከሚያዉኩ ተግባራት የመቆጠብ፤

በ. ለጥሪት ማፍሪያ እንዲሆነው በልዩ ውሳኔ የተሰጠውን የጋራ መኖሪያ ቤት ከተሰጠዉ ቀን ጀምሮ አስር ዓመት እስኪሞላዉ ድረስ በማንኛዉም መንገድ ለሌላ አካል ያለማስተላለፍ፣

ተ. ቤቱ ከተረከበ በኋላ የሚመጡ ወጪዎችን በራሱ የመሸፈን፣

ቸ. የጋራ መኖሪያ ቤት ተጠቃሚዉ በዚህ መመሪያ በሚሰጡ ቤቶች ከአንድ ጊዜ በላይ ተመዝግቦ የኮንደምኒየም መኖሪያ ቤት ወስዶ ከተገኘ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የወሰዳቸውን ቤቶች  የማስረከብ፣ ለተጠቀመባቸዉ ወራቶች በሚወጣዉ የቤት ኪራይ ተመን መሰረት የመክፈል እና ለሰጠው የተሳሳተ መረጃ በህግ ተጠያቂ የመሆን፤

ኀ. ተጠቃሚዎች ባል እና ሚስት ሆነዉ በየስማቸው የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንደሚኒየም/ ውስደው ቢገኙ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሁሉንም ቤቶች የመመለስእና ለተጠቀመባቸዉ ወራቶች በሚወጣዉ የቤት ኪራይ ተመን መሰረት የመክፈል እና ለሰጠው የተሳሳተ መረጃ በህግ ተጠያቂ የመሆን፤

ነ. ተጠቃሚዉ ከትዳር ጓደኛው ጋር ፍቺ የፈጸመ ከሆነ ፍቺው የተፈጸመው ከስድስት ወር በፊት ስለመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ቅሬታ አቀራረብ፣ ተጠያቂነት እና ሥራ ላይ ስለመዋል

### 12. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት

በሚሰጡ አገልግሎት ቅሬታና አቤቱታ ያለው የጋራ መኖሪያ ቤት /የኮንድሚኒየም/ ተጠቃሚ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወይም በአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መመሪያ መሰረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

### 13.ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተካተቱ ጉዳዮችን ተላልፎ የተገኘ አግባብ ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 14.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም አካል ይህን መመሪያ ለመፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 15. ስለትርጉም አሰጣጥ

በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጹ ጉዳዮች ትርጉማቸዉ አሻሚ ሆኖ ከተገኘ ኮሚሽኑ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 16.ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 17.መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወይም በአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 18.መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ነሀሴ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡